የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ
DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA
OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አርባምንጭ መጋቢት ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 41
Arbaminch March 14 2023

አዋጅ ቁጥር ፵፬/፪ሺ፲፮ ዓ.ም
የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የጫት ኤክሳይዝ ታክሰ --- ገጽ

Proclamation No 44/2024
The South Ethiopia Regional State Chat Excise Tax -- page

## አዋጅ ቁጥር ፵፬/፪ሺ፲፮ ዓ.ም
## የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የጫት ኤክሳይዝ ታክሰ

### መግቢያ

በክልሉ ውስጥ የጫት ፍጆታ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመሄዱ ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ የሚያግዝ የታክስ ስርዓት ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በጫት ላይ የሚከፈለውን ታክስ አሰባሰብ ፍትሃዊነት ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የክልላችን የኢኮኖሚ ዕድገት ከደረሰበት ደረጃ ጋር የተጣጣመ እና የኢኮኖሚውን ዕድገት የሚያግዝ ዘመናዊና ቀልጣፋ የግብር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

## Proclamation No 44/2024
## The South Ethiopia Regional State Chat Excise Tax

### Preamble

WHEREAS, it has become necessary to introduce a tax system to discourage the Regional consumption of chat which is growing at higher rate;

WHEREAS, it is necessary to ensure equity in the collection of the tax payable on chat;

WHEREAS, it is necessary to establish a modern and efficient tax system that is compatible with the level of economic growth of our Region and helps the economic development:

NOW, THEREFORE, the South Ethiopia Regional Council has issued this proclamation in accordance with Article 54 sub Article 3 of the constitution of the Region.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፵፬/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩) **"ክልል"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነው፤

፪) **"ቢሮ"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ገቢዎች ቢሮ እና እንደአግባብነቱ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ መምሪያዎች፣ ጽ/ቤቶች እና የታክስ ማዕከላትን ይጨምራል፤

፫) **"ታክስ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በክልሉ በሚካሄደው የጫት ግብይት ላይ የሚከፈል የጫት ኤክሳይዝ ታክስ ነው፤

፬) **"ታክስ ከፋይ"** ማለት የጫት ኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ነው፤

፭) **"የጫት ግብይት ማዕከል"** ማለት ጫትን ከመነሻው ወይም ከማምረቻ ስፍራው ወይም ለግብይት አማካይ በሆነ ስፍራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለግብይት ማካሄጃ እንዲሁም ታክስ መሰብሰቢያነት የሚያገለግል የታጠረ ወይም በበረንዳነት የተዘጋጀ ወይም እንደ አካባቢው ሁኔታ የተከለለ ስፍራ ነው፤

## Part One
## General

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as " the South Ethiopia Region Chat Excise Tax Proclamation No.44/2023"

### 2.Definitions

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1) "**Region"** means South Ethiopia Region;

2) "**Bureau"** means the Revenue Bureau of the South Ethiopia Region as well as the departments and office at each administration level;

3) **"Tax"** means the excise tax payable on chat transaction in the Region in accordance with this Proclamation;

4) **"Tax payer"** means a person liable to pay chat excise tax;

5) **"Chat trading center"** means a fenced or especially prepared place where chat is processed and tax collected from the source or the place of production to an average place for trading together with the relevant parties;

**፮)** **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ቢሆንም ባይሆንም ማንኛውም ድርጅት ነው፡፡

**፯)** የጾታ አገላለጽ፡ በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴት ጾታም ያገለግላል፡፡

**፫. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በክልሉ ውስጥ ጫት በማምረት ወይም ለገበያ በሚያቀርብ በማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፬. ታክስ የመክፈል ግዴታ**

ጫትን በይዞታው ስር በማድረግ፣ በማጓጓዝ ወይም በማንኛውም መንገድ ለሽያጭ የሚያቀርብ ሰው በዚህ አዋጅ የተወሰነውን ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

**፭. የታክስ ማስከፈያ ልክ**

በክልሉ ውስጥ ተመርቶ ጥቅም ላይ የሚውልና ወደ ሌላ አካባቢ የሚጓጓዝ ጫት በአንድ ኪሎ ግራም ብር 18.00 /አስራ ስምንት ብር/ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል፡፡

**፮. የታክስ ማስከፈያ ቦታ**

የጫት ኤክሳይዝ ታክስ በቢሮው የሥራ ቦታ የሚሰበሰብ ሲሆን ቢሮው እንደ አስፈላጊነቱ የሚመረትበት ወይም የግብይት ማዕከል እንደ ኤክሳይዝ ታክስ መሰብሰቢያ ማዕከልነት ሊገለገልበት ይችላል፡፡

**፯. ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት**

በዚህ አዋጅ መሠረት በጫት ላይ የተጣለውን ኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበስበው ቢሮው ይሆናል፡፡

6) **"Person"** means a natural person or an organization whether it is juridical person or not.

7) **Gender Expression፡** Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. Scope of Application**

This proclamation applies to any person who produces or markets chat within the Region.

**4.Duty to Pay Tax**

Any person, who possesses, transports, carries or offers chat for sale in any manner shall be liable to pay the tax levied in this proclamation.

**5. Rate of the Tax**

Chat Regionally produced, consumed and to be supplied for sale or destined for sale shall be charged at a tax rate of Birr 18 (Eighteen Birr) per kilogram.

**6. The Place of Tax Collection**

The excise tax on chat is collected at the Bureau's workplace, and the Bureau can be used as a production or marketing center as needed, as well as an excise tax collection center.

**7. The Power to Collect Tax**

The tax levied under this Proclamation shall be collected by the revenue Bureau.

**፰. ማህበራትን ስለማደራጀት**

ሀ/ ቢሮው ጫትን ከማሳው፣ ከመነሻው ወይም ከግብይት ማዕከላት የሚገዙትን ወይም በማንኛውም መልኩ በጫት ግብይት የሚሳተፉትን አካላት፤ ከንግድና ገበያ ልማት እና ከግብይትና ህብረት ሥራ ተቋማት ጋር በመተባበር በማህበር የሚደራጁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

ለ/ ማህበራቱ ከተደራጁ በኋላ በቢሮው ተመዝግበው ወደ ሥራ ይገባሉ፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፱. የግብይት ማዕከላት**

በጫት ምርት መነሻ ወይም ለጫት ግብይት አማካይ በሆኑ አካባቢዎች ቢሮው የጫት የግብይት ማዕከላትን ከግብይትና ህብረት ሥራ እንዲሁም ከአስተዳደር አካላት ጋር በመቀናጀት ያቋቁማል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፲. ስለንግድ ፈቃድ**

ማንኛውም በጫት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው አስፈላጊውን የግብር ቅድመ ሁኔታ በማሟላት የንግድ ፈቃድ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

**፲፩. ሌሎች ታክሶችን የመክፈል ኃላፊነት**

ማንኛውም በጫት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ግብር ከፋይ በዚህ አዋጅ ከተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ በተጨማሪ በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች መሠረት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

**8. Organizing Cooperatives**

A. The Bureau, in cooperation with trade and market development and trading and cooperative institutions, shall facilitate the organization of associations for those who purchase chat from the field, from the source or from trading centers, or who are involved in the trading of chat in any way.

B. After the cooperatives are organized, they shall be registered with Bureau and begin their work. The details shall be determined by directives.

**9. Marketing Center**

The Bureau shall establish chat marketing centers in areas that are the place of chat production or intermediate for chat trading in coordination with marketing and cooperatives as well as administrative bodies. The details of enforcement shall be determined by directives.

**10. About Business License**

Any person engaged in the chat business is required to obtain a business license by meeting the necessary tax requirements.

**11. Duty to Pay Other Taxes**

A tax payer liable to pay the tax levied under this Proclamation shall, in addition to excise tax, pay other direct and indirect taxes as determined by other applicable laws.

**፲፪. የወንጀልና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ተጠያቂነት**

የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደራዊና የወንጀል ጥፋቶች በተመለከተ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፳፪/፪ሺ፲፮ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**፲፫. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም አሰራር፣ ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፬. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ቀደም ሲል የጫት ግብርን ለማስከፈል በወጣው ህግ መሠረት መክፈል ሲገባው ያልተከፈለ ታክስ በዚህ አዋጅ መሠረት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

**፲፭. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ሀ/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

ለ/ ቢሮው ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ከጸደቀበት መጋቢት ፭ ቀን ፪ ሺህ ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አርባምንጭ መጋቢት ፭ ቀን ፪ሺ፲፮**

**ጥላሁን ከበደ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር**

**12. Criminal and Administrative Accountability**

The provisions of Tax Administration Proclamation No. 22/2023 shall apply regarding administrative and criminal offenses related to the excise tax on chat.

**13. Inapplicable Laws**

Any law or practice that is inconsistent with this Proclamation shall not apply to matters covered by this Proclamation.

14. **Transitory Provision**

The unpaid tax that was previously due under the law enacted to levy the tax on chat shall be collected according to this proclamation.

15. **Power to Issue Regulation and Directive**

A.The Regional Administrative Council may issue regulations necessary to implement this Proclamation.

B.The Bureau may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued under sub-article (1) of this Article.

16. **Effective Date**

This Proclamation shall be effective from March 14/2023, approved by the South Ethiopia Region State Council.

**Done at Arba Minch 14th Day of March 2023**

**TILAHUN KEBEDE**

**President of The South Ethiopia Regional State**